ያኮበኮበ ዳሽ ፋይፍ አይሮፕላን አለ:: ብር ያጨቁበትን ቦርሳ እንጠልጥለው ወደሱ የሚሮጡ ይመስላሉ:: ከካርቱን ስእሉ ግርጌ የተፃፉት መፈክሮች:-

«ትንሽ ትንሽ እንድማ! አንድ ሰውና አንድ መሳሪያ እስከሚቀረኝ ድረስ እዋጋለሁኝ» የሚል ነው:: ሰልፈኛው ያሰማው የነበረው መፈክር ደግሞ:-

«የዝምባብዌ መንግስትና ህዝብ ፈርጣጩንና ፋሽስቱን መንግስቱ ሀይለማርያምን ለኢትዮጵያ ህዝብ አሳልፎ መስጠት አለበት! የሀገርን ሀብት የዘረፉ ባስቸኳይ ለፍርድ ይቅረቡ!» የሚል ነው::

ተጥመልምለን የባህል አዳራሹን እንዳለፍን ጋዜጠኞች ፎቶ ለማንሳት፣ በቴሌቪዥን ለመቅረፅ ይሯሯጡ ጀመር:: ልክ ጣላይ አደባባይ ስንደርስ ቦታ በታችንን ይዘን ቆምን:: ይዘናቸው ከነበሩት መፈክሮች ውስጥ:-

- የብሄሮችና የብሄረሰቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት የዲሞክራሲ መብት ነው!
- ኢህአዲግ የሰላምና የዲሞክራሲ ዋስትና ነው!
- ህዝባችን የተጠማውን ሰላም ያገኝ!
- የሰላምና የዲሞክራሲ ኮንፈረንስ የኢትዮጵያ ህዝብ ምጥ የወለደው ነው!
- የተጎሳቆለችውን አገራችንን መልሰን እንገነባለን!
- የህዝቡ የበላይነት ይከበራል! የሚሉ ናቸው::

የክብር እንግዶች መጥተው ቦታቸውን እንደ ያዙ የሰልፉ አዘጋጅ ኮሚቴ ሰብሳቢ የመግቢያ ንግግር አድርገው ፕሮግራሙን ለሚመራው መኮንን ለቀቁለት:: ከዚህ በኋላ በተከታታይ ሶስት ግጥሞች ተነበቡ:: ሁሉም ግጥሞች ከብሶት የመነጩ ነበሩ:: አቅራቢዎቹም ወጣት መኮንኖች ናቸው:: ከጨለማ ህይወት ላይ መውደቃቸውን ግጥሞቻቸው ይጠቁማሉ:: ተስፋን እያጭሩም! ያስቆዝማሉ እንጅ::

ሁሉም ነገር ተብሎ ካበቃ በኋላ የማእከሉ ሀላፊ ንግግር ለማድረግ ሲነሱ ለክብራቸው ርችት ተተኮሰላቸው:: ወዲያው እርጭ ሲል መናገር ጀመሩ:: ባማረኛ ነበር የተናገሩት:: መነፀር አድርገዋል:: የቀይ ዳማ ናቸው::

"... ወደፊት በዚህ ማእከል ውስጥ ላጭር ጊዜ በምትቆዩበት ወቅት ጥሩ ጥሩ ተግባራትን ታከናውናላችሁ ብለን እንገምታለን..." በቃ ይኸው ነው:: ሌላው ስለሽግግር መንግስቱ፣ ስለቻርተሩ አላማ ነው:: ይኸ ደግሞ ምናችንም አይደል:: በዚሁ የሰልፉ ፍፃሜ ሆነ::

ይች "አጭር ጊዜ ቆይታ" የምትለዋ አባባል የሁላችንንም ጭንቅላት በጥብጠዋለች:: ለሶስት ቀናት ሴሚናር ተብለን ሆለታ ገብተን ይኸውና ሰስተኛ ወራችንን ይዘናል:: ይች አጭር ጊዜ ደግሞ ትረዝም ይሆን?



# 25

ጉድ አይመጣ የለም እያደር ጉድ መጣ፣
«እመኑ» ተባልነ አምነን ብንመጣ::

ሲሲቲን ሲዘንብ ነው ያደረው:: ከነጋም በኋላ ካፊያ ቢጤ ነበር:: እየቆየ ግን ፈተት እያለ መጣ:: የጣላይ ያየር ፀባይ ይኸው ነው:: ይዘንብና ወዲያው ፀሀይ ትወጣለች:: ከዚያ ደግሞ ጭቃው ምጥጥ ይላል:: ታዲያ ይኸ የዋልካ ጭቃ ስንረግጠው እንደ ካትራሚ ንክስ ንክስ ያደርግና ወዲያው ተተምትሞ ሀስፋልት ሆኖ ቁጭ ያላል:: ሲዘንብ ደግሞ ሙልጭልጭ ይልና አፍርጦ ይጥላል:: ዛሬስ አፍርጦ የጣለን የኢህአዲግ ነገር ነው:: እያደር ከበደን፣ ሰልፍ ተሰልፈን እንጀቱን እናራራስን ብለን ነበር፣ እሱ ግን ሽቦ እንጀት ሆነ:: እንደ ኩራን ብንቀመጥ ይሻለን ነበር:: በመሰለፋችን ያላሰብነውን መዘዝ መዘዙብን:: አውቀነዋል፣ አጭሯን ጊዜ ለማስረዘም ነው::

ዛሬ ስብሰባ እንደ ምናደርግ የተነገረን ማታ ነበር:: ያው እንደ ሁልጊዜው በየሻለቃችን ነው የተሰበሰብነው:: አዳራሹ ጢም ብሎ ሞልቶ የመስኮቱ ዙሪያ እንደ አጥር ክርችም ብሏል::

የነጭ ሽንኩርት ሽታ እንጀት ያማስላል፤ አፍንጫን ይቆርጣል:: ሲዘንብ ስላደረ ነው መሰል የሙቀቱ መጠን ቀነስ ያለ ነው:: የሲጋራው ጭስ ግን የማርፈጃውን ጉም ተክቶ ወደ ኮርኒሱ ይበናል:: ተጠራቅሞ ካፊያ እንዳይሆን እንጅ...

ታጋይ ሀጎስ ጉሮሮውን ጠራረገና "ዛሬ የተሰበተብንበት ምክንያት ባለፈው ያካሄድነውን ሰልፍ ለመገምገም ሲሆን ዋናው ትኩረታችን ግን 'የበደልነውን ህዝብ መልሰን እንክሳለን!' የሚለውን መፈክር ሳትይዙ በመቅረታችሁ ሰልፉ የተሟላና ከልብ ነበር ለማለት አንችልም:: ስለዚህ ዛሬ ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ተወያይተን የዚህን መፈክር ፅንሰ ሀሳብ ተረድታችሁና አምናችሁ ካወጣችሁት ያቋም መግለጫ ጋር ተጨምሮ ይተላለፋል" ሲል አብራራልን:: ለካም ያቋም መግለጫው በሬዲዮ ያልተላለፈው ለዚህ ነው:: ቤቱ በግለት እጁን አወጣ:: ላንድ ሻምበል እድል ሰጠው::

"በመጀመሪያ ለምጠይቅህ ጥያቄ ተገቢ መልስ ስጠኝ፣ ለመሆኑ ሰልፉ የኢህአዲግ ነው የኛ?" ሲል ጠየቀው::

"ሰልፉ የኢህአዲግ አይደለም፤ የናንተ ነው:: ሆኖም ግን የመቆጣጠር ሀላፊነት አለብን" ሲል መለሰለት::

"በመቆጣጠሩ በኩል ያላችሁን ድርሻ እኛም እንቀበለዋለን:: ሰልፉን ግን የጠየቅነው እኛ እስከሆንን ድረስ የምንይዘውንም መፈክር መወሰን ያለብን እኛ ነን:: በርግጥ እናንተን የሚፃረር መፈክር እንዳንይዝ መከልከል ትችላላችሁ:: ይህም ቢሆን የዲሞክራሲን መርህ ይፃረራል:: ነገር ግን እናንተ የምትፈልጉትን መፈክር እንዴት እንሸከማለን?" በማለት ተናግሮ ተቀመጠ:: በርካታ መኮንኖች ደግሞ እጃቸውን አወጡ:: ሀጎስ ለማንኛውም እድል ሳይሰጥ እራሱ:-

'ኑሮ ኀመዘዘኝ አጅጉን ገለማኝ፣
የትስ አቤት ልበል ጨኸቴን ማን ይሰማኝ፣
ጧት ማታ መዋጮ አንጀቴን አወጣኝ፣
ይኸ አልበቃኝ ብሎ ልጄንም አምጣሉኝ።
እኔ መኢገማ፣ ሚስቴ አኢሴማ፣ ልጄ አኢወማ፣
ፈጣሪ ግደለኝ ይህንን ሳልሰማ።' ይል ነበር።

"ይህ ሁሉ ድርጊት ሲፈፀምበት እኛ እናውቅ ይሆን? ለምልመላ የተሰማራን መኮንኖችስ የለንም?

"የኢትዮጵያ ህዝብ የደም እንባ እያነባ፣ በርሃብ እንደ ቅጠል እየረገፈ ደርግ ኢሰፓን በመሰረተበት ወቅት ከተማዎችን በቀይ ጨርቅና ባንፑል በኮሪያ ኤክስፐርቶች ያሸበርቅ ነበር። ያዲስ አበባ አረጃጅም ፎቆች በቀይ ጨርቅ ተሸልመው ከተማዋ በተለያዩ ቀለማት ባጌጡ አፑሎች ስትብረቀረቅ በዚያን ወቅት መሬት ላይ ያለን ይመስለን ነበር? በርግጥም አልነበረንም። ተፈጥሮን በቁጥጥራችን ስር አድርገን እንጨፍር ነበር። ይህንም ህዝቡ በዝምታ አላለፈውም:-

'በደርግ ጊዜስ ሁሉም ተደበረ፣
ግንኙ ሳይቀር ቀይ ጨርቅ ለብሶ እያደረ።'

"ደርግ ህዝቡን የተስፋ ዳቦ እያስገመጠ እሱ በውስኪና በጮማ በመቀማጠሉ ከዛሬ ነገ ያልፍልኝ ይሆናል በማለት በችግር የተጠበሰው ህዝብ በኢህድሪ ምስረታ ወቅት ተስፋው በመሟጠጡ:-

'እነሱው ደግሰው እነሱው በሉት፣
መቼም አያምርበት የባለጌ ቤት' ብሏቸዋል።

"ደርግ ግን ቢነግሩት የሚገባው አይደለም። ልክ ከቋጢኝ ድንጋይ ላይ ውሀ እንደ ማፍሰስ ይቆጠራል። ወይንም 'ደንቆሮ ቢጠቅሱት መልሶ ይጠቅሳል፣ ለምን ቢባል እሱ ስለማይሰማ ሌላው የሚሰማ ስለማይመስለው ነው።' እውነትም የድንቁርናው ድንቁርና (አብሪትም ሊሆን ይችላል) የኢትዮጵያን ህዝብ በካኪ አንገቱን አነቀው። ህዝቡ አሁንም ደርግን ከመንነተል ወደ ኋላ አላለም:-

'ደርግ ተራመደ ሄደ ገሰገሰ፣
ባስራ አንድ አመቱ 'ጥልቆ ለበሰ።' ብሎታል።

"የደርግ እብሪት እንዲህ በዋዛ የሚታለፍ አይደለም። 'መንደር ምስረታ' ብሎ ባወጣው ፖሊሲ መሰረት የኢትዮጵያን ህዝብ ቤቱን እንዲያፈርስ አደረገው። ያለ ጥናት፣ ያለ እቅድ አጋርፋ በሰለጠኑ የገበሬ መሀንዲሶች እየተቀየሰ ገበሬው በእድሜው ያነፃቸው ቤቶች 'አሞራው ቡድን' የሚባል አቋቋም ጣራው እየተገነበረ እንዲወድቅ ተደረገ። ይህንም ገበሬው በምሬት ሲገልፀው:-



'እርሻ አነሰኝ ብዬ ስቆጣ ስቆጣ፣
እዩት ተመልከቱት የባሰ ቀን መጣ፣
ቤት እያፈረሰ የሚያባርር መጣ።
መሬታችን አንኩ፣ እህላችንን አንኩ፣ ልጆቻችን አንኩ፣
የሬሳችን መውጫ ቤታችንን አትንኩ።'

ብሎ አልቅሷል።

"እንዲህ ያለውን ሰው በላ ስርአትና መንግስት ነበር ለአስራ ሰባት አመታት ተሸክመን ያቆየነው። ታዲያ ህዝቡ የደም እንባ ሲያነባ እኛ መለዮ ለባሽ ልጆቹ ደርሰንለታል? ከደርግ መንጋጋ አላቀነዋል? የኢትዮጵያ ህዝብ ግፍ መች በዚህ ብቻ ያከትምና:-

"እህል ሰብል ገበያ ድርጅት ወይም 'እሰገድ' የተባለ አቋቋሞ ገበሬ ያመረተውን ምርት እንዳሻው እንዳይሸጥ ሽማች ግብረ ሀይል በየገጠሩ በማሰማራት እርሶ አደሩን ገፎታል። በዚህም ገበሬው ዝም አላለም:-

'እረ እነዚህ ደርጎች ጤፍ አምጡ፣ ቅቤ አምጡ ይላሉ፣
ቅቤ የት ተገኝቶ በሀይለስላሴ ተቀልጦ ተበልቶ' ብሏቸዋል።

"አዎን፤ የደርግ መፈጠር ህዝቡ አንገሽግሾት አንቅሮ የተፋውን የሀይለስላሴን አስተዳደር እንደገና እንዲናፍቀው አስገድዶታል። ቢልም አይፈረድበት። ባይሆን ያኔ የሚስቱ፣ የልጆቹ፣ የቤቱ ባለቤት ነበር። የኔ የሚለው ነበረው። የደርግ እብሪት በዚህም አልተገታ። ከተሜውን መኪናውን እሁድ እሁድ እንዳያንቀሳቅስ በህግ አገደው። ህዝቡ ቢጨንቀው የጋብቻ ቀኑን ወደ ቅዳሜ አዛወረ። ይህም አዲስ ታሪክ ነበር።

"የኢትዮጵያ ህዝብ አንድ አፄ መሸከም አቅቶት ሲንቀጠቀጥ መቶ ሀያ አፄዎች ተሸከም ተብሎ ተፈረደበት። ያውም መንጋ ደናቁርት። እረ መቼ ይሆን እንባው የሚደርቀው? እረ መቼ ይሆን ባገሩ ኮርቶ የሚኖረው? እስከመቼስ ያንባገነኖችን ጡጫ ችሎ ይኖራል? ፍርዱን ለዚያው ሲቃይተኛ ህዝብ እተወዋለሁ።

"ቀደም ሲል አንድ መኮንን 'ለደርግ መቆየት ኢህአዴግ አስተዋፅኦ አድርጎለታል' ያሉትን እኔም አምንበታለሁ። ለምን ቢባል የኢህአዴግ አቋም ባለመታወቁ ህዝቡ ኅሰኝነትን አጥብቆ ስለሚቃወም ደርግ ይህን አጋጣሚ በመጠቀም 'ገንጣይ፣ አስገንጣይ፣ ጎጠኛ፣ ወያኔ...' እያለ በፕሮፖጋንዳ ወጥሮ በመያዝ ለድሜው መራዘም ፋታ እንዲያገኝ አግዞታል። እንዲያውም ባንድ ወቅት አዲስ አበባ ይወራ የነበረው 'ደርግ ያለ ኢህአዴግ፣ ኢህአዴግም ያለ ደርግ አይኖሩም' እየተባለ ነበር።

"መታወቅ ያለበት ግን ደርግ ይህን ሁሉ ግፍ ሲፈፅም የመጀመሪያው ግፍ የተፈፀመበት ይህ ሰራዊት መሆኑን ነው። በመጨረሻም ውድቀታችን የከፋና አሳፋሪ ሆኖ 'እመት' እየተባልን እንወገጣለን። በከብ ጠረጴዛ መሆኑ መልካም።

"የኢትዮጵያን ህዝብስ 'አልበደልንም' ብለን እንከራከር ጥሩ፤ ታዲያ የኢትዮጵያን ህዝብ ልጆች ነን ካልን መንግስቱና መሰሎቹ

ሲፈረጥጡ ለምን ፍርክስክሳችን ወጣ? ለምን የሳምንት እድሜ እንኳን አልመከትንም? እውነት ከዚህ ሁሉ መኮንን መካከል አንድ ወይም ከዚያ በላይ አሞት ያለው ጠፍቶ ነው? ልብ ያለው ከሌለ ደግሞ ያሁኑ ክርክር መነሳት የለበትም:: ያሉንን ከመፈፀም ሌላ ምርጫ የለንም:: እኔ እንደ ሚገባኝ የኢትዮጵያን ህዝብ በድለነዋል ባይ ነኝ:: ታዲያ እኔ ኢህአዲግን ብሆን ከዚህ አስቀምጬ የርዳታ እህል እየለመንኩ አልቃልብም ነበር:: ሱሪውን አስወልቁ ቀሚስ እያስጠለቁ፣እንዝርት አስጨብጨ 'ሂዱ ከሚስቶቻችሁ ጋር ጥጥ ፍተሉ' ነበር የምለው::

'ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልሆነ እንዳባቱ፣
አመልማሎ ይፍተል ቁጭ ብሎ እንደናቱ!'

ይላሉ አበው:: አመሰግናለሁ::" ብዬ ስቀመጥ ቅልጥ ያለ ጭብጨባ ተጨበጨበ:: ለምን እንዳጨበጨቡ ግን አልገባኝም:: ማጨብጨብ ልማድም ስለሆነ ይሆናል::

ሀንስ ሲጋራውን እያያዘና ሁለት ጊዜ ምጎ "መቶ አለቃ ጥሩ ተናግረው በስተመጨረሻ ብቻ ያልሆነች ሀሳብ ሰንዝረው ነው የተቀመጡት:: የሆነ ሆኖ ጥቅል ሀሳባቸው 'በድለናል' የሚል ስለሆነ በሳቸው ሀሳብ የምትስማሙ እጃችሁን አውጡ" ሲል ጠቅላላ እጅ ወጥቶ ጨራሮ መሰለ::

"ተቃውሞ?" ሲል ጠየቀ:: ከተቀመጠበት ተነስቶ ቆሞ ነበር:: አንድም መኮንን የተቃወመ አልነበረም:: በዚሁ "የበደልነውን ህዝብ መልሰን እንክሳለን!" ብለን ተገላገልን::

ጤፍ አምጡ፣ ቅቤ አምጡ፣ ልጅ አምጡ በማለት ያስቃየናችሁ፣
ዛሬ ማሩን ስንል ማሩን አባካችሁ::

ምሳ ላይ የሞገዲድና የሸፈዲድ አባላት በየሻለቃው የተካሄዱትን የውይይት ውጤቶች በሙሉ አዘነቡልን:: ካንደኛ ክፍለ ጦር አንደኛ ብርጌድ ሶስቱም ሻለቆች አምነዋል:: ከሁለተኛ ብርጌድ አንደኛ ሻለቃ ያለምንም ችግር "የበደልነውን ህዝብ መልሰን ለመካስ ዝግጁ ነን:: ይኸ ደግሞ ምን ችግር አለው?" ብለው ነው ባንድ ድምፅ የተስማሙት:: ሺፈዲድ ግን ውሳኔአቸውን አንኳሷል:: ሞገዲድ ደግሞ ግንዛቢያቸውን አድንቋል::

እኔ ባለሁበት ሁለተኛ ሻለቃ ያው ስንዳረቅ ብንውልም በመጨረሻ አምነናል:: ከኛ ብርጌድ ውስጥ አምፆ ያለው ሶስተኛ ሻለቃ ነው:: ከምሳ በኋላም ስብሰባው ይቀጥላል:: ሸፈዲድ ያነሷቸውን ነጥቦች አድንቆላቸዋል:: "ኢህአዲግ እንደ የፖለቲካ ድርጅት እንጅ የኢትዮጵያ ህዝብ የወከለው መንግስት ባለመሆኑ በሱ አንጠየቅም:: የኢትዮጵያን ህዝብ እንዱ ጨራሽ ኢህአዲግ ስለሆነ ተጠያቂው አይጠይቀንም" የሚሉ ሀሳቦች ተሰንዝረዋል:: ሶስተኛ ብርጌድ ሶስቱም ሻለቆች ተጨፋጭፈው ተጨፋጭፈው በመጨረሻ አምነዋል::

ሁለተኛ ክፍለ ጦር ደግሞ ካንዱ ብርጌድ ውስጥ አንዱ ሻለቃ ብቻ ሲያምን የቀሩት ግን አንሞከርም ብለዋል:: እንዲያውም ሁለት



ሻለቆች ታጋዮችን ካዳራሽ አባረዋል:: እነዚህን ሻለቆች ሸፈዲድ እጅግ ሲያደንቃቸው ሞገዲድ ግን «ስርአት አልበኞች» ብሏቸዋል::

ምሳየን በልቼ እንዳበቃሁ በቀጥታ እየገሰገስኩ የሄድኩት ሶስተኛ ሻለቃ አዳራሽ ነበር:: መቀመጫ ቀርቶ መቋሚያም አልነበረም:: ከሰአት በፊት ያመኑት መኮንኖች ለማዳመጥ አዳራሹን አጨናንቀውታል:: በስተመግቢያው በር በኩል ስርስሬ በመግባት ደረቴን ገልብጬ ቆምኩኝ::

ከሰአት በፊት ሻለቆቻቸውን ያሳመኑት ታጋዮች ተሰብስበዋል:: እየተቀባበሉ በመደሰክር መኮንኑን አደነዘዙት:: መኮንኑ በነገርም፣ በሙቀትም እየዛለ መጣ:: ከሰአት በፊት ያመኑት ሻለቆች ይህን ሻለቃ ተስፋ አስቆረጠውታል:: ታጋዮቹ ተናግረው ተናግረው ሲያልፍላቸው አንድ መኮንን ብድግ አለና:-

"አብዛኛው ጦር አምኗል:: ስለዚህ የኛ መንገታገት ዋጋ የለውም:: እንመንና እንገላገል" ሲል ቤቱ በመስማማት አጨበጨበ:: ታጋዮቹም ያሸናፊነት ኩራት ተሰማቸው:: ፈገግ አሉ::

"አሁንስ መቶ አለቃ ተስማማህ?" አለው ሰብሳቢው ታጋይ ወንዳንድ ወጣት መኮንን አትኩሮ እያየ::

"በርግጥ እኔ እንደ ጥፋት ሆኖ ያገኘሁት በወታደርነቴ መንግስት የሚያወጣቸውን መመሪያዎች ተቀብዬ ተግባራዊ ማድረጌ ነው:: ዛሬ እንዲህ መጠየቁን ባውቀው ኖሮ ያንዬ ስታዘዝ እንቢ ብዬ መረሸን ነበረብኝ" ብሎ ሲናገር አንድ መኮንን ገንፍሎ በመነሳት:-

"እንዲህ ያሉትን ሀሳበ ግትሮች እየወሰዳችሁ በግል አሳምኑልን:: ይኸ መቶ አለቃ ቢነግሩት የማይገባው ነው:: ከሰአት በፊትም እሱው ነው ጎትሮን የዋለው!" በማለት በቁጣ ተናግሮ ተቀመጠ::

"አሁንስ?" አለው ታጋዩ::

"አሁን አምኛለሁ:: ያመንኩት ግን ተገድጀ እንጅ በሀሳብ ተረትቼ አይደለም:: ከኛው መካከል ተወስጀ ለብቻየ እንዳምን ሀሳብ ስለተሰጠብኝ ነው" አለ ከፍተኛ ቅሬታ ተሰምቶት::

"እስቲ አምነናል የምትሉ እጃችሁን እውጡ?" ሲል ጠቅላላ እጅ ወጣ:: ሁሉም አመኑ ማለት ነው:: ከዚህ በኋላ የስብሰባው ፍፃሜ ሆነ::

አንደኛ ክፍለ ጦር እንግዲህ በሙሉ አመነ ማለት ነው:: ሁለተኛ ክፍለ ጦር ደግሞ ያላመኑትን ለማሳመን ስብሰባው ከሰአት በኋላም እንደ ቀጠለ ስለሆነ ወደዚያው እየገሰገስኩ ሄድኩ:: እየተጣደፍኩ የገባሁት አራተኛ ብርጌድ አንደኛ ሻለቃ አዳራሽ ውስጥ ነበር:: እነዚህ ደግሞ በዕሁፍ አጠቃለው ነው ያቀረቡት:: አንድ መኮንን ጥቅል ሀሳቡን ቁሞ በንባብ ሲያሰማ ነበር የደረስኩት::

«1ኛ. በማሸነፍ በትር ስልጣኑን የጨበጠው ኢህአዲግ በመሆኑ በኛና በሱ መካከል የተፈጠረው የጦርነት እልቂት እራሱን ከተጠያቂነት ለማዳን ሲል፣ የኢትዮጵያን ህዝብ 'በድለናል' በሉ ማለቱ አግባብ ስላልሆነ በዳይም ተበዳይም ህዝብ ሳይሆን ሁለቱ ጦርነቱን ያካሄዱት ወገኖች ናቸው:: ስለዚህ እንበድልም እንበድልም 3ኛ ጠያቂ ሀይል እስቲ ፈጠር ድረስ ባንቸኩል ጥሩ ነው::

«2ኛ. የምስራቁ ጦርነት ዳርድንበርን ለማስከበር ስለሆነ በዚህ ጦርነት ወቅት ተበድያለሁ የሚል ካለ በማእዘን ተለይቶ ይቅረብ::

«3ኛ. 'ተበድለናል' የሚለው ጥያቄ የኢትዮጵያ ህዝብ ጥያቄ ከሆነ በህዝቡ በኩል ይቅረብ::

«4ኛ. ዲሞክራሲ ሲባል የመናገር፣ የመፃፍ፣ የመደራጀት፣ የመከራከር ሙሉ መብት ሲሆን እኛ ግን ያለንበት ሁኔታ ስለማይፈቅድልን ለማመንም ሆነ ለማሳመን ወይንም ተመጣጣኝ መልስ ለመስጠት አንችልም:: ብንችልም እንኳን የምንሰጠው ሀሳብ ያቋም መለኪያ ተደርጎ ስለሚወሰድ የዲሞክራሲ ነፃነት የሚለው ቃል በዚህ ስብሰባ ላይ ወይንም ጨርሶ በዚህ ማእከል ውስጥ መነሳት የለበትም» የሚሉ ነበሩ:: በነዚህ ነጥቦች ላይ ከፍተኛ ፍጭት ከተካሄደ በኋላ ያው «ሌሎቹ ካመኑ የኛ ብቻ መነታረክ ምን ዋጋ አለው» ብለው አመኑ::

መከንኑ ለልጆቹ፣ ለሚስቱ ሲል የማይከፍለው መስዋእትነት የለም:: ልጆቹና ሚስቱ ይጎትቱታል:: በሌላ በኩልም በጅምላ መታጎራችን በብዙ መንገድ ጎድቶናል:: ከእስር ያመለጠው ታማኝነቱን በመግለጽ፣ ኢህአዲግን አሞጋግሶ ከንፁህን ጋር ንፁህ ተብሎ መለቀቅ ይፈልጋል:: ነፍስ የገደሉ፣ ገንዘብ የመዘበሩ ደግሞ አድፍጠው ከጅምላው ጋር ተቀላቅለው መሽሎክ ይፈልጋሉ:: ምንም የሌላቸው ድሆች ደግሞ ከኢህአዲግ ጥግ ለማግኘት ሲሉ ጅራታቸውን ይቆላሉ:: በዚህ ምክንያት አንድነት የለንም:: ያለ ጠባቂ ቂጥ ለቂጥ ስንጋፋ እንውላለን:: በዚህ ላይ በጎሳ መከፋፈል ተጀምሯል:: ይህ የጎሳ ጉትቻ የት እንደሚያደርሰን ግን አላወቅነውም::

# ምእራፍ አስር

በረባው ባረባው ጆግና ደግናው ሙቶ፣
መንጋ ለከስካሳ እንቶ ፈንቶው ቀርቶ፣
ስም አልባ ልንሆን ነው ስማችነን ጠፍቶ::

## 26

እንቁራሪቶች ይሽከመከማሉ:: ደግሞ ይተዛዘላሉ:: መተቃቀፋቸው ይሆን? በተለይ ከመሸ በኋላ በነሱ እልልታ ድንቁር ነው የምንለው:: ፋታ የላቸውም:: በጊዜአቸው፣ በወቅታቸው እልል ይበሉ እንጂ...

ባለፈው ስብሰባችን የበደልነውን ህዝብ መልሰን እንክሳለን ካልን ወዲህ አዲስ ነገር ብቅ ያለው ካዲስ አበባ፣ ከወሊሶ፣ ከወልቂጤ ሴቴ ላጤዎች፣ ሊስትሮዎች፣ በራሪ ነጋዴዎች ተነቅለው መምጣታቸው ነው:: ተስፈኞች ደግሞ ከበቾና ከሊሙ ሰቃ ገንፍለው መጥተዋል:: ደግሞ ህፃናት ናቸው:: በያንዳንዱ ሻለቃ የምግብ አዳራሽ በምሳ ሰአትና በራት ወቅት መጥተው ከበሩ ላይ ይሰፍራሉ:: በዚህ የተነሳ ዛሬ ጦላይ በሰው ተጨንቃለች:: በማእከሉ ውስጥ አዳዲስ ንግድ ቤቶች እንደ እንጉዳይ እየፈሉ ናቸው:: ሻሂና ቡና አፍሊዎች በየጥጋጥጉ፣ በየዛፉ ስር ቁጭ ቁጭ በማለት የቅምጥ ገበያ ጀምረዋል:: አንደኛ ክፍለ ጦር፣ አንደኛ ብርጌድ አጠገብ፣ «ታይዋን» ተብሎ ተሰይሟል:: የማይሸጥ ነገር የለም:: በተለይ ሽንኩርት፣ ቃሪያ፣ ሰንደል፣ ወረቀት... ይዘው እንደ ዝንጀሮ ጠባቂ ይጎለታሉ መከንኖቹ::

በየሻለቃው መኖሪያ ክልል ውስጥ ለውስጥ ደግሞ በረንዳው ሁሉ ሻሂና ቡና እየተፈላ መሸጥ ተይዟል:: ይህ እንግዲህ የሰፈር ገበያ መሆኑ ነው:: የሚንስ ቤት ሰራተኞችም በፈረቃቸው ተኳኩለው ቡናና ሻሂ ችርቻራ ገብተዋል:: ሁሉም የኛን ኪስ ለማራገፍ ሽሚያ ይዟል:: የሰከረ አሳ ሆነናል:: ስካር ብል ስካር ትዝ አለኝ::

ስካር ከሆለታ ወዲህ ትንሽ ፋታ ሰጥቶን ነበር:: ይህን ሰሞን እንደገና ተቀስቅሶ ከዋዩ በድጋፍ ካምፕ መግባት ተይዟል:: አረቂ ከወልቂጤ በጆሪካን በቀን የሚያመላልሱ አራት ሳንድሮቨሮች አሉ:: እኛ ዋዩ እየሄድን መገልበጥ ነው:: ባለፈው ሰሞን አንድ መኮንን ከመጠን በላይ ጠጥቶ በመስከሩ ውሃ ውስጥ ገብቶ ሙቷል:: ሞት ባነሳ የሞቱት ሁሉ ታወሱኝ:: ነፍሱን ይማረውና መቶ አለቃ ሀይለሚካኤልንም እየረሳሁት ነው:: ለነገሩማ እንኳን የሞቱት ያለነው እየተረሳን ነው::

ሌላው ከሰሞኑ የተከሰተው አዲስ ነገር የድርጅት ጋጋታ ነው:: በሽፈዲድና በሞገዲድ ስንማረር ሌሎች በህቡእ ይንቀሳቀሱ የነበሩት አሁን ዲሞክራሲ በሚገባ በመስፈኑ ፕሮግራማቸውን ይፋ አድርገው ካምፑን ያተራምሱታል::

1ኛ. አገልግል መንትፍ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት (አመዲድ)
2ኛ. አገልግል ጠላፊ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት (አጠዲድ)
3ኛ. ሚስት ነጣቂ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት (ሚነዲድ)
4ኛ. ፖስታ ቀዳጅ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት (ፖቀዲድ)
5ኛ. ኪስ ዳሳሽ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት (ኪዳዲድ) ናቸው::

አመዲድና አጠዲድ ካንድ ላይ ተዋህደው ለመስራት ቃል ገብተዋል:: ምክንያቱም በፕሮግራማቸው ላይ ምንም አይነት ልዩነት የለም:: ኪስ ዳሳሽና ፖስታ ቀዳጅ ትንሽ ልዩነቶች ስላሏቸው በህብረት ለመስራት ወስነዋል:: ሁሉም ድርጅቶች ግን ፕሮግራማቸውን ይፋ ከማድረጋቸው በፊት በተግባር ብዙ ድርጊቶችን አከናውነዋል:: አሁን በቅርቡ ፕሮግራሙን ይፋ ያደረገው ኪዳዲድ የተባለው ድርጅት አስደናቂ ተግባር በመፈፀሙ የተነሳ በርካታ አባላትን ለማፍራት ችሏል::

ነገሩ እንዲህ ነው:: ያንድ መኮንን ሚስት ባሏን ለመጠየቅ ካዲስ አበባ መጣች:: ያንዱ ቤተሰብ ሲመጣ ተሰባስበን ማጫወት፣ ስላዲስ አበባ መጠየቅ ባህላችን ነው:: በመሆኑም አንድ የኪዳዲድ ስራ አስፈፃሚ አባል ጠጋ ይልና ፍትፍቱንም፣ ወሬውንም ሲፈተፍት ያመሻል::

ሚስት ለባሏ "ጓደኛህ መቶ ብር ልኮልሃል" ትልና ከቦርሳዋ ውስጥ አንዲት ሌላ ትንሽ ቦርሳ ታወጣና "እንካ" ትለዋለች:: ባልም ለሚስቱ አሳቢ ኖሮ ጓደኛውን አመስግና "እኔ ለጊዜው ችግር የለብኝም:: አንቺ ልጆች ይዘሽ ስለሚቸግርሽ ላንቺ ይሁንሽ" ይላታል:: ሚስትም ችግር ኖሮባት ኖሮ ሳታንገራግር መልሳ ከሚጢጢ ቦርሳዋ ከታ እሷን ደግሞ ከትልቁ ቦርሳዋ ክትት ታደርጋለች:: እጅሬ ኪዳዲድ እይት::


ከመብል፣ ከመጠጥ፣ ከጨዋታ በኋላ በየካምፖችን ለንግዳ ማረፊያ ብለን የፀጉር ቤቶችን፣ የልብስ መተኮሻ የነበሩትን [illegible]ጃጆችን

"ልክ ነው፤ እግዚአብሔር ይጠብቃታል!" አለኝ:: ከዚያም "ለጤናችን" ብለን የድራፍት ብርጭቆዎቻችንን አንስተን በማጋጨት ተጎነጨን::

"እንዲያውኮ ጎርፉ! ያለፍንበትን ሂደት መለስ ብዬ ሳስበው ይደንቀኛል፤ እጣብቂኝ የበዛበት፣ ሰው በሰው ላይ ተራምዶ፣ ጓደኛውን አሳልፎ በመስጠት ራሱን ለማስገበት የተፍጨረጨረበት የክፉ ፈተና ጊዜ ነውኮ ያሳለፍነው" አለ በድሉ ተከዝ ብሎ::

"መቼም ከሰነበትን የወደፊቱንም በጊዜው እናየዋለን፤ ተስፋ የማደርገው ግን ከኛ ውድቀት አዲሱ ትውልድ ትምህርት ያገኛል ብዬ ነው" ስለው ቀበል አደረገና:-

"ከኛ ውድቀት ካልተማረማ እንደኛው ወይም በባሰ ሁኔታ ጊዜ ያስተምረዋል::" አለኝና ድራፍታችንን እየጨለጥን በየባእታችን ተጓዝን...



ካሁን ቀደም ያሳተማቸው መጻሕፍት:-
1. ዳር እስከዳር፣
2. ጥቁር ደም፣
3. ጥልፍልፍ::

ደራሲው መ/አ አንዳርጌ መስፍን

«... አገር እናት ነች፤ አገር ሚስት ነች፤ አገር ልጅ ነች፤ አገር ሀብት ነች፤ ሲያገኙ መደሰቻ፣ ሲያጡ መተከዣ፣ ሲሞቱ መቀበሪያ:: ያለአገር ምንም ነገር የለም...»

«... ለመሆኑ የጎሳ መሪዎች ምን ያስቡ ይሆን? ሰው ወይስ ወንበር? አገር ወይስ መንደር? የትኛው ነው መቅደም ያለበት?...»

«... ሆዳም ሰው ከሆዱ ሌላ አገርም፣ ዘመድም የለው... በሆዱ ብቻ እየተገዛ ውርደትን ክብሩ አድርጎ ይኖራል!...»

«... እኔ ባባቴ ጎንደሬ፣ በናቴ ትግሬ ነኝ፤ ባለቤቴ ግማሽ ኦሮሞ፣ ግማሽ ደግሞ አደሬ ናት:: የኛ ልጆች የየትኛው ብሔረሰብ አባል ሊሆኑ ነው?...

«... እንዲያው ይኸ ሠራዊት ሲመለመል ባፈሳ፣ ሲረሽን ባፈሳ፣ በርድ ሲወጣ በመንጋ፣ ሲሸሽ በጅምላ፣ በመጨረሻም እጅ ሲሰጥ እየተሻማ በጠቅላላ ሆነ!...»

ዋጋው 6.50